**NAFYAD SCHOOL**

# 2 SAMPLE MODEL EXAM. FOR GRADE 8 CHEMISTRY 2

መመሪያ ፡- ቀጥሎ ለተሰጡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ከተሰጡት አራት ምርጫዎች በመምረጥ መልስ መስጫ ወረቀትህ ላይ በማጥቆር መልስ/ሽ

1. ኬሚስትሪ በጤና ዘርፍ ውስጥ ሊሰጥ የሚችለው ጥቅም የቱ ነው።
   A. ፀረ-አረምን ለማምረት B. ሲምንቶ ለማምረት C. ፕላስቲክን ለማምረት D.መድሐኒትን ለማምረት
2. ኮስቲ ሶዳ እና ሞራን እንደ ጥሬ እቃነት የሚጠቀመው የኬሚስትሪ ውጤት የቱ ነው?

   A. ሲሚንቶ B. መድሐኒት C. ወርቅ D. ሳሙና

3. የምግብ ጨው በውስጡ ሶድየም እና ክሎሪን ይዟል። ይሄ አረፍተ ነገር የሚገልፀው

   A. የምግብ ጨውን መዋቅሩን B. ለውጡን C. ይዘቱን D. ጥቅሙን

4. ከሚከተሉት ኬሚካሎች መካከል በኢትዮጵያ ውስጥ የሚመረተው የቱ ነው?

   A. $HNO_3$ B. $NH_3$ C. $H_3PO_4$ D. $Al_2(So4)_3$

5. ስለ ልዩ ቁስ ግንኙነትና የተለያ የጉልበት ዓይነቶች እንደ ብርሃን፣ ሙቀትና የኤሌክትሪክ ጉልበት የሚያጠኑ የተቀናጁ

   የተፈጥሮ ሳይንስ ዘርፎች የትኞቹ ናቸው?

   A. ባዮሎጂና ፊዚክስ B. ኬሚስትሪና ፊዚክስ C.ጂኦሎጂና ኬሚስትሪ D. ባዮሎጂና ኬሚስትሪ

6. ከሚከተሉት አካላዊ ባህርያት መካከል (ሊለኩ)ሊሰፈሩ የማይችለው የቱ ነው ?

   A. ጣዕም B. ነጥብ ቅልጠት C. እፍጋት D. ነጥበ ፍሌት

7. ከሚከተሉት መካከል ኬሚካላዊ ለውጥን የማያሳየው የቱ ነው?

   A. ዝገት B. መቃጠል C. የወተት መኮምጠጥ D. የውሃ መፍላት

8. የአልሙኒየም ንጥረ ነገር ይዘቱ $30Cm^3$ እና መጠነ ቁሱ 240g ቢሆን እፍጋቱ ስንት ይሆናል?

   A. 8 $^g/cm_3$ B. 12 $^g/cm_3$ C. 270 $^g/cm_3$ D. 7200 $^g/cm_3$

9. ድብልቆችን ለመለየት ከሚረዱ ዘዴዎች ውስጥ ጥሊያን ምንጠቀመው ለየትኛው ነው?

   A. ጨውን ከውሃ B. አልኮልን ከውሃ C. የአይረን ዱቄትን ከአሸዋ D. አፈርና ውሃ

10. ከሚከተሉት ውስጥ ዋህደዘር ድብልቅ የሆነው የቱ ነው?

A. ደም B. ወተት C. አየር D. አፈር

11. ከሚከተሉት ውስጥ ፈሳሽ ብረት አስተኔ የሆነው የቱ ነው?

A.ሜርኩሪ B.ኦክስጅን C.አለሙኒየም D. ካልሲየም

12. ከሚከተሉት ውስጥ ባለ ሁለት አቶም ንጥረ ነገር የሆነው የቱ ነው?

A.ኦክስጅን B. ሃይድሮጂን C. አርጎን D. A እና B.

13. ከሚከተሉት ውስጥ የኮባልት ውክል የሆነው የቱ ነው?

A. CO B. Cu C. CO D. Ca

14. በማግኒዚየም ሰልፌት ($MgSO_4$) ውሰጥ ስንት ንጥረ ነገሮች አሉ?

A. 2 B. 3 C. 4 D. 5

15. ከሚከተሉት ውስጥ በትክክለኛው የውህድ ቀመር የተፃፈው የቱ ነው?

A. አይረን (III) ኦክሳይድ = $Fe_2O$ B. ሜርኩሪ (II) ኦክሳይድ HgO

C. ሊድ (II)ኦክሳይድ =$PbO_2$ D. ኮፐር (I) ኦክሳይድ = CUO

16. ከዚህ በታች ያለው ኬሚካላዊ እኩልታ ሶመጣጠን የዚንክ ጠቋሚ ቁጥር የሚሆነው የቱ ነው?

$Zn + HCl \rightarrow ZnCl_2 + H_2$

A.1 B. 2 C.3 D. 4

17. ከሚከተሉት ውስጥ ባለብዙ አቶም አዮን ያልሆነው የቱ ነው ?

A. $OH^-$ B. $NO^-3$ C. NaBr D. $CO3^{2-}$

18. የአንድ ንጥረ ነገር ውክሉ “ $^y_xA$” የ “y’’ ምልክት ምንን ያሳያል?

A. አቶማዊ ቁጥር B. አቶማዊ መጠነ ቁስ C. የኤሌክትሮን ቁጥር D. የፕሮቶን ቁጥር

19. ከሚከተሉት መሰረታዊ ቅንጣጢቶች ውስጥ በኒውክለስ ውስጥ የሚገኝ አዎንታ ሙል ያለው የቱ ነው?

A. ኤሌክትሮን B.ኒውትሮን C. ኒውክለስ D. ፕሮቶን

20. ከሚከተሉት ንጥረ ነገሮች መካከል የኤሌክትሮን ቅመጣው 2፣8፣6 የሆነው የቱ ነው

A. $_{13}Al$ B. $_{15}P$ C. $_{16}S$ D. $_{12}Cl$

21. ከሚከተሉት ውስጥ ስለ ደልተን አቶማዊ ቲዎሪ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

A. ንጥረ ነገሮች የተገነቡት ከአቶሞች ነው

B. አቶም የተገነባው ከፕሮቶን ኒውትሮን እና ኤሌክትሮን ነው

C. የአንድ ሁለት እና ከዛ በላይ የሆኑ ንጥረ ነገር ሲፀገበሩ በትንሽ ወደር የሚገለፁ ውህድ ይፈጥራሉ

D. የአንድ ንጥረ ነገር አቶም ከሌላ ንጥረ ነገር አቶም የተለየ ነው

22. የ "N'' ምህዋር ሊሸከም የሚችለው ከፍተኛ የኤሌክትሮን ቁጥር ስንት ነው?

A.2 B. 8 C. 32 D. 18

23. የአለሙኒየም አዮን $_{13}Al^{3+}$ ትክክል የሆነው የቱ ነው?

A. 10 ፕሮቶኖች አለው B. 13 ኤሌክትሮን አለው C. 13 አቶማዊ መጠነ ቁስ አለው D. 10 ኤሌክትሮኖች አለው

24. ከሚከተሉት አቶሞች መካከል አይሶቶፕ የሆኑት የትኞቹ ናቸው?

A. $^{12}_{6}c$ እና $^{13}_{6}c$ B. $^{35}_{17}Cl$ እና $^{37}_{18}Cl$ C. $^{1}_{1}H$ እና $^{1}_{2}H$ D. $^{15}_{7}N$ እና $^{15}_{7}N$

25. አቶማዊ ቁጥር 12 የሆነ ንጥረ ነገር በአርኬ ሰንጠረዥ ውስጥ በስንተኛ አምድና አርኬ ውስጥ ይገኛል?

A. በአምድ IIA እና በ 3 ተኛ አርኬ B. በአምድ IIIA እና በ 2 ተኛ አርኬ

C. በአምድ IA እና በ 2 ተኛ አርኬ D. በአምድ IVA እና በ 3 ተኛ አርኬ

26. ከሚከተሉት መካከል 9 አቶማዊ ቁጥር ካለው ጋር ተመሳሳይ ባህሪ ያለው የንጥረ ነገር አቶማዊ ቁጥር ስንት ነው?

A. 17 B. 15 C. 12 D. 10

27. በአርኬያዊ ሰንጠረዥ ውስጥ በአምድ ውስጥ ከላይ ወደታች የሚቀንሰው ባህሪ የቱ ነው?

A. ኒውክላዊ ሙል B. አቶማዊ መጠን C. የብረት አስተኔያዊ ባህሪ D. የኢብረት አስተኔ ባህሪ

28. በውጫዊ ምህዋራቸው ውስጥ 7 ኤሌክትሮኖች የያዙ ንጥረ ነገሮች ምን ይባላሉ?

A. ሀሌጂን B. ግዑዝ ጋሶች C. አልካሊ አስተኔያዊ ባህሪ D. የኢብረት አስተኔ ባህሪ

29. የካልስየም የኤሌክትሮን ቅመጣ 2፣8፣8፣2 ቢሆን ቫላንስ ኤሌክትሮን ስንት ነው?

A. 8 B. 2 C. 20 D. 10

30. በአርኬያዊ ሰንጠረዥ ውስጥ አምድ (II)A እና አምድ (III) መካከል የሚገኙ ንጥረ ነገሮች ምን ይባላል?

A. ቋሚ ንጥረ ነገሮች B. ግኡዝ ጋዞች C. የሽግግር ንጥረ ነገሮች D. የአልካሊ ብረት አስተኔዎች

31. የአልካሊኖት አጠቃላይ ቀመር የሆነው የቱ ነው?

A. CnH2n B. CnH2n+2 C. CnH2n+6 . CnH2n-2

32. ከሚከተሉት ውህዶች ውስጥ ተከታታይ ቤተሰብ(homologoues)የሆነው የቱ ነው?

A. $CH_2$፣$C_3H_4$፣$C_4H_8$ B. $C_2H_4$ ፣$CH_2$ ፣$C_2H_6$ C. $C_3H_6$ ፣$C_5H_{10}$፣ $C_6H_8$ D. $H_2$ ፣$C_2H_4$፣ $C_3H_6$

33. ከሚከተሉት ውስጥ ካርቦናማ ያልሆነው የቱ ነው?

A. ኢቴን B. የምግብ ጨው C.ኢታኖል D.ሚቴን

34. ከሚከተሉት ውህዶች ውስጥ ቤዛማ ኦክሳይድ ያልሆነው የቱ ነው?

A. CaO B. MgO C.$CO_2$ D.$Fe_2O_3$

35. ከሚከተሉት ውስጥ የስነ-ህይወት ናሙናን ሳይበሰብስ ለማቆየት የሚያገለግለው የትኛው ነው?

A. ኢታኖል B. ዴኬን C.ቬኔጋር D. ፎርማሊን

36. ከሚከተሉት ውህዶች ውስጥ አሲድ የሆነው የቱ ነው?

A. $H_2CO_3$ B. $Ca(OH)_2$ C. NaCl D. $MgCO_3$

37. ከሚከተሉት ኬሚካላዊ እኩልታዎች ውስጥ ግላዊ አፀግብሮት የሆነው የቱ ነው?

A. $AgNO_3 + HCl \rightarrow AgCl + HNO_3$ B. $Mg + 2HCl \rightarrow MgCl_2 + H_2$

C. $Na + H_2O \rightarrow NaOH + H_2$ D. $NaOH + HCl \rightarrow NaCl + H_2O$

38. ከሚከተሉት ውስጥ የብረት አስተኔ ባህሪ ያልሆነው የቱ ነው?

A.ኤሌክትሪ አስተላላፊነት B. መመዝመዝ C.ማቃጨል D. ይሰባበራሉ

39. ከሚከተሉት ውስጥ የአለሙኒየም ብረት አዘል ማዕድን የሆነው የቱ ነው?

A.ቦክሳይት B. ማግኔታይት C.ሀላይት D. ሄማታይት

40. የኮፐርና የዚንክ ቅይጥ ብረት አስተኔ ምን ይባላል?

A. ብሮዝ B.ብራስ C.ሶልደር D. ዱላሚን

41.ከሚከተሉት የብረት አስተኔ ቡድኖች ውስጥ በተፈጥሮ ነፃ ሆነው የሚገኙት የትኞቹ ናቸው?

A. Na፣ Ag፣ Au B. Cu ፣Ca ፣Ag C. Cu፣ Ag ፣Au D. Fe፣ Ag ፣Au

42. ከሚከተሉት ውስጥ ሶዳ አሽ በመባል የሚታወቀው ውህድ የቱ ነው?

A. $Na2CO_3$ B. $Na2SO_4$ C. NaOH D. NaCl

43. ከሚከተሉት ብረት አስተኔዎች ውስጥ ቀላልና ጠንካራ የሆነው የቱ ነው?

A. Na B. Fe C. Al D. k

44. ከኢብረት አስተኔዎች ውስት ኤሌክትሪክ አስተላላፊ የሆነው የቱ ነው?

A. ግራፋይት B. ሰልፈር C.ፋሊረንስ D. ዳይመንድ

45. ከሚከተሉት ውስጥ ሁለቱ የሰልፈር ካልሮርሞች የትኞቹ ናቸው?

A. ነጭና ቀይ B. ሮምቢክና ሞኖክሊክ C. ዳይመንድ እና ግራፋይት D. ጠጣርና ፈሳሽ

46. ከሚከተሉት ውስጥ ካልሮርም የሌለው የቱ ነው?

A. ናይትሮጂን B. ኦክስጅን C. ሰልፈር D. ካርቦን

47. የፎስፈረስና ሰልፈርን ንጥረ ነገሮች ያገኘው ጀርመናዊ ኤሚስት ማን ይባላል?

A. ሄኒንግ ብራንድ B. ዳንኤል ረዘርፎርድ C. ጆን ደልተን D. አርስቶትል

48. ከሚከተሉት ውስጥ ፈሳሽ ኢብረት አስተኔ የሆነው የቱ ነው?

A. ካርቦን B. ሰልፈር C. ብሮሚን D. ፎስፈረስ

49. የፎስፈረስ ዋነኛው ጥቅም የሆነው የቱ ነው?

A.ሲሚንቶ ለማምረት B.መስታወት ለመስራት C. ማዳበሪያ ለማምረት D.ቀለም ለማምረት

50. ከሚከተሉት ውህዶች በውሃ ውስጥ በመገኘት ጊዜያዊ የውሃ ኢ-አረፋማነት የሚያመጣ የቱ ነው?

A. $CaSO_4$ B. $NaHCo_3$ C. Ca $Cl_2$ D. $MgSO_4$

51. የድፍድፍ ነዳጅ ውጤት ያልሆነው የቱ ነው?

A. ናፍጣ B. የድንጋይ ከሰል C. ኬሮሲን D. የሲሊንደር ጋስ

52. ከሚከተሉት ውስጥ እንደ ዋና ዋና እፅዋት አልሚ ምግብ የማይታየው የቱ ነው?

A. ናይትሮጂን B.ኦክስጅን C. ፖታስየም D. ፎስፈረስ

53. ከሚከተሉት መካከል ለውሃ ብክለት ምክንያት ሊሆን የማይችለው የቱ ነው?

A. ለእርሻ የምንጠቀምባቸው ኬሚካሎች B. ክሎሪን ውሀ ውስጥ መኖር

C. አሲዳማ ዝናብ D. ከኢንዱስትሪ የሚወጡ ፈሳሾች

54. ከአፈር ምንዝሮች መካከል ጠጣር ካርቦናማ ልዩ ቁሶች እና ማዕድናት ድርሻ በመቶኛ ስንት ነው?

A. 50% B. 75% C. 25% D.12.5%

55. ቤዛማ አፈርን አስመልክቶ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

A. ከ 7 በላይ PH አለው B. በደረቃማ አካባቢ የሚገኝ አፈር ነው

C. ከ 7 በታች PH አለው D. በውስጣቸው $OH^-$ አለው

56. ከሚከተሉት ጋዞች ውስጥ የግሪን ሃውስ ጋስ የሆነው የቱ ነው?

A. CO B. $SO_2$ C.$O_2$ D. $CO_2$

57. የማግኒዢየም ሰልፌት ($MgSO_4$) ቀመራዊ ክብደት ስንት ነው?

A. 100 B, 130 C. 120 D. 121

58. በ 27 ግራም አሉሚኒየም ውስጥ ስንት ሞሎች አሉ?

A. 1 B, 3 C. 4 D. 5

59. በሰልፈር ትራይ ኦክሳይድ($SO_3$) ውስጥ የሰልፈር መጠን በመቶኛ ስንት ነው?(አቶማዊ ክብደት S=32 O=16)

A. 40 B, 25 C. 75 D. 50

60. ከሚከተሉት ውስጥ ብዙ አቶሞችን በውስጡ የያዘ የቱ ነው?

(አቶማዊ ክብደት H=1,C=12,O=16,Cl=35.5)

A. 48g ኦክስጅን B. 71g ክሎሪን C,18g ካርቦን D. 2g ሀይድሮጂን